በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ

<u>አጋርፋ</u>

ጉዳዩ፡- **<u>የኮሌጁን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ</u>**

<u>የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል</u>፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 36 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 16 ገጽ አባሪ በድምሩ 52 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል፡፡ በመሆኑም በገጽ 53 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

☞ ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከ52 ገጽ አባሪ ጋር

☞ ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከ52 ገጽ አባሪ ጋር

<u>አዲስ አበባ</u>

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

ግንቦት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር
በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት
የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት የተጠቃለሉ የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል።

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱና የኮሌጁ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው።

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን የሚያካትተው፦ -

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በተዘጋጁት የተጠቃለሉ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት መሰረት የሚሆኑትን የሂሳብ መግለጫዎች የማዘጋጀት ኃላፊነት የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.1/3/7 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ኮሌጁ የካቲት 29 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ሚ7/000/777/02099 በጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. **የገቢ ሂሳብ**

   1.1. **ከሽያጭ ሂሳብ ላይ አለአግባብ የተቆረጠ የቅድሚያ ግብር (ዊዝሆልዲንግ)፤**

      1.1.1. **ግኝት**

      በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 30 ተራ ቁጥር 2(ሀ) መሰረት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግብር ነጻ መሆናቸው ተደንግጓል። ሆኖም ኮሌጁ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከመሆኑም በተጨማሪ ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ የንግድ ትርፍ ግብር የማይመለከተው ሆኖ ሳለ ኮሌጁ ከደቡብ ምርጥ ዘር ድርጅት ጋር ምርጥ ዘርን ለማባዛት በገባው ውል ስምምነት መሠረት ኮሌጁ ካገኘው ገቢ ብር 609,226.87 ውስጥ ድርጅቱ 2% የቅድሚያ ግብር ብር 12,184.53 ቀንሶ ያስቀረ መሆኑ ታውቋል።

      1.1.2. **ሥጋት**

      ህጉን ሳይከተሉ ክፍያ መፈጸም፡-

      - መንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ሊያደርገው ይችላል።
      - የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

      1.1.3. **የማሻሻያ ሃሳብ**

      ኮሌጁ ህጉን ሳይከተል የፈጸመውን የቅድሚያ ግብር ክፍያ ተመላሽ አስደርጎ ፈስስ ማድረግ ይኖርበታል።

1.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የደቡብ ምርጥ ድርጅት ቆርጦ ያስቀረውን 2% የቅድሚያ ግብር ብር 12,184.53 ተመላሽ እንዲያደርግ የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 2/1-12/0544 ለድርጅቱ ተገልጿል።

2. ተሰብሳቢ ሂሣብ

2.1 በደንቡና በመመሪያው መሠረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

2.1.1. ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና ኮሌጁ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ ከካፒታልና ከውስጥ ገቢ በጀት በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 7,172.95፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 12,910.00፣
- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 3,767.40፣

በድምሩ ብር 23,850.35 በደንቡና በመመሪያው መሰረት ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ ስለሁኔታው ቀደም ባሉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲወራረዱ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ሳይወራረዱ (ሳይሰበሰቡ) ይገኛሉ፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

2.1.2 ሥጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ፡-

- የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ ገንዘቡ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል።
- ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም።

2.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ መደረግ እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. በካፒታል በጀት በ4203 የሂሳብ መደብ የተያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 7,172.95 በቀጣይ ተጣርቶ ምላሽ የሚሰጥበት ይሆናል።
2. ከብር 12,910.00 ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፣
   2.1. መምህር ሲሳይ ከበደ ተብሎ እንዲስተካከል እየገለጽን ብር 9,500.00 (ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ) ለምርምር ሥራ ወስዶ የምርምር ሥራው ባለመጠናቀቁ ምክንያት ሂሣቡ አልተወራረደም።

   2.2. መምህርት አስካለች ደሳለኝ ክሊራንስ ሳያዞሩ ኮሌጁን የለቀቁና ለውሎ አበል የወሰዱትን ሂሳብ ብር 3,410.00 እንዲያወራርዱ ክትትል እየተደረገ ሲሆን በቀጣይ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል።

3. ከውስጥ ገቢ በጀት በ4203 የሂሳብ መደብ የተያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 3,767.40 ከአቶ የኋላሸት ገብሬ የሚፈለግ ሲሆን ግለሰቡ ከሀገር ውጪ ጠፍተው የሄዱ ስለመሆኑ በማጣራት እና ለኮሌጁ ሥራ አመራር ቀርቦ ከመዝገብ እንዲሰረዝ በተደረገው መሠረት ከእዳ እንዲሰረዝ ጥር 10 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 1/2/1-103/0774 በተጻፈ ደብዳቤ አመራር ተሰጥቶበታል።

2.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲወራረዱ እየተደረገ ያለው ጥረት እንዲቀጥል፤ መወራረድ (መሰብሰብ) የማይችሉ ሂሳቦች ደግሞ ደንቡና መመሪያውን

ተከትለው እንዲሰረዙ እንዲደረግ እያሳሰብን የተሰረዘው ሂሳብ አግባብነትና ትክክለኛነት ግን በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።

3. ተከፋይ ሂሣብ

3.1 ለረጅም ዓመታት በተከፋይ የተያዘ ሂሳብን በተመለከተ፤

3.1.1. ግኝት

በኮሌጁ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ኮሌጁ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከካፒታልና ከውስጥ ገቢ በጀት በ5002 የተከፋይ ሂሳብ ኮድ (መደብ) ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ ብር 3,161.40 የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።

3.1.2. ሥጋት

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

3.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ መደረግ ይኖርበታል። የማይከፈሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል።

3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተከፋይ የተያዘውን ብር 3,161.40 በቀጣይ አጣርተን ምላሽ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

4. መደበኛ የሒሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ሂሳቦች፤

4.1. የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦች፤

4.1.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት የገቢ፣ የወጪ፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይና የመሳሰሉት ሒሳቦች

የዴቢት ወይም የክሬዲት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰብሳቢ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ የሚታየው ከወጪ ቀሪ መድረሻ ሚዛን (Ending Balance) በዴቢት መታየት ያለበት ቢሆንም በብር 2,054.55 ክሬዲት ሚዛን፤ የተከፋይ ሂሳብ ደግሞ ክሬዲት ሚዛን ማሳየት ያለበት ቢሆንም ብር 2,047.16 ዴቢት ሚዛን አሳይቷል፡፡ (ለዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል)

4.1.2. _ሥጋት_

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ በየሒሳብ መደቡ የተመለከቱትን ሂሳቦች ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

4.1.3. _የማሻሻያ ሃሳብ_

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል።

4.1.4. _የሥራ አመራሩ ምላሽ_

የሂሣብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን ማስተካከያ እናደርጋለን።

5. _የወጪ ሂሣብ_

5.1. _በመረጃ ያልተደገፈ የሂሳብ ማስተካከያ_፤

5.1.1. _ግኝት_

በኮሌጁ የተከናወኑት የሒሳብ ማተካከያዎች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የተከተሉ መሆኑን እንዲሁም የሂሳብ ማስተካከያዎቹን አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በብር 82,954.55 በሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ (ጆርናል ቫውቸር) ላይ በዴቢትና በክሬዲት የሂሳብ ማስተካከያ የተሰራ ቢሆንም ማስተካከያዎች ላይ ስህተቱ በየትኛው የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀሙ እና የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት ያልተገለጸ በመሆኑ

ምክንያት የማስተካከያ ሒሳቡን ትክክለኛነትና አግባብነት ለማረጋገጥ አልተቻለም። (ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

5.1.2. ***ሥጋት***

የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁም ስህተቱ በየትኛው የገቢና የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ ሳይገለጽ (ሳይታወቅ)የሚሰሩ የሂሳብ ማስተካከያዎች ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ ሊከፍቱ እና የሒሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጣቸው ይችላሉ።

5.1.3. ***የማሻሻያ ሃሳብ***

በፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያው መሰረት ለተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች ተገቢው መረጃ ሊቀርብላቸው ይገባል።

5.1.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

ለተሰሩት የሂሣብ ማስተካከያዎች በተሰጠው አስተያየት መሠረት ለወደፊቱ ማስተካከያዎቹ ያስፈለጉበትን ምክንያት እንገልጻለን።

5.2. **በትክክለኛው (በተገቢው) የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤**

5.2.1. ***ግኝት***

ኮሌጁ የወጪ ሂሳቦችን የሚመዘግበው የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለተለያዩ ክፍያዎች የተፈጸመው ብር **16,400.00** በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል።
(ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

5.2.2. ***ሥጋት***

- የሂሳብ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ከበጀት በላይ ወይም ከበጀት በታች ጥቅም ላይ የማዋልን ችግር ለማጣጣም የተመዘገበ መሆኑን ሊያመላክት ይችላል፡፡

5.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በስህተት ለተመዘገቡት ሂሳቦች ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራላቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በትክክለኛው (በተገቢው) የሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሣብ የልዩ ቁርጥ አበል ክፍያ በሂሣብ መደብ ኮድ 6116 መክፈላችን ስህተት መሆኑን በተሰጠን አስተያየት የምናስተካክል ቢሆንም ቀደም ሲል ባለን ግንዛቤ መሠረት የቁርጥ አበል ክፍያ በበጀት ኮድ 6116 ላይ ይከፈላል የሚል ግንዛቤ ያለንና በዚህ በጀት አመትም በዚሁ በጀት ኮድ ላይ በጀት ተይዞ ክፍያው እየተፈጸመ ያለ በመሆኑ ለሚቀጥለው በጀት አመት በተገቢው የበጀት ኮድ ላይ በጀት እንዲያዝና ክፍያውንም በበጀት ኮድ 6121 ላይ እንዲሆን የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

5.3. በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተፈጸመ የግንባታ ሥራ ክፍያ፤

5.3.1. ግኝት

በኮሌጁ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በግዥ መመሪያው እና በውሉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና የአመዘጋገብ ሥርዓቱም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ የመማሪያ ህንጻና የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታ ሥራን እንዲያከናውን ከቤዛ ኮንስትራክሽን የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር እንዲሁም የዶርሚቴሪና የምድረ ጊቢ ግንባታ ሥራን እንዲያከናውን ከ3 ኤም ኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ ለመሆናቸው ኦዲት ሲደረግ ቀጥለው የተመለከቱት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

1. **<u>ቤዛ ኮንስትራክሽን የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ</u>**

- ብር **441,804.29** በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መኖሩ፣
- ብር **687,888.01** በብልጫ የተቀነሰ የቅድሚያ ግብር ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር **3,617,462.64** ያልተመለሰ (ያልተቀነሰ) የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
- ከላይ በተመለከቱት የሂሳብ ልዩነቶች ምክንያት ብር **2,487,770.34** በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ መኖሩ፣

2. **<u>3ኤም ኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር</u>**

- ብር 171,062.14 በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መኖሩ፣
- ብር 609,963.04 በብልጫ የተቀነሰ የቅድሚያ ግብር መኖሩ፣
- ብር 1,220,812.98 ያልተመለሰ (ያልተቀነሰ) የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
- ከላይ በተመለከቱት የሂሳብ ልዩነቶች ምክንያት ብር 439,787.80 በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ መኖሩ፣

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 5 እና 6 ተያይዟል)

5.3.2. <u>ሥጋት</u>

በአመዘጋገቡ ላይ በሚታየው ስሕተት ምክንያት፡-

- ☞ የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።
- ☞ ሊቀነስ የሚገባው ገንዘብ ሳይቀነስ ሊቀር ይችላል።
- ☞ መከፈል የሌለበት ገንዘብ ሊከፈል፤ መከፈል ያለበት ገንዘብ ደግሞ ላይከፈል ይችላል።
- ☞ ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን
- ☞ ይችላል።

5.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በአመዘጋገብ ላይ ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ፤ መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ እንዲሰበሰብ፤ መከፈል ያለበት ገንዘብ እንዲከፈል፤ ለወደፊቱም በኮንስትራክሽን ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

5.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በፋይናንስ መመሪያው መሠረት ያልተመዘገበና ያልተፈፀመ የግንባታ ሥራ ክፍያ ላይ የታዩ ስህተቶችን እንደገና በማጣራት በአመዘጋገብ ላይ ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ የምናደርግ ሲሆን መከፈል ያለበት ገንዘብ እንዲከፈል፤ መሰብሰብ ያለበት ሂሣብ እንዲሰበሰብ እና በኮንስትራክሽን ግንባታ ክፍያ ዙሪያ ያለብንን የሙያ እጥረት የተሻለ አፈጻጸም ካሳዩ ድርጅቶች የልምድ ልውውጥ በማድረግ የመጨረሻ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ማስተካከያ የምናደርግ ይሆናል፡፡

5.4. ከውል ሥምምነት በላይ ተከፍሎ የተገኘ የአማካሪ ክፍያ፤

5.4.1. ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16(17) መሰረት ኮሌጁ ለፈጸማቸው ግዥዎች ተገቢ ውል የሚፈጽም መሆኑንና የከፈላቸውም ክፍያዎች በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

1. ኮሌጁ ከኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር (Construction Design S.C.) ጋር በፈጸመው የማማከር አገልግሎት ውል መሰረት ብር 1,857,181.90 መክፈል ሲገባው እስከ ሰኔ 30, 2010 ዓ.ም ድረስ ብር 4,025,000.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

2. የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ከኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር (Construction Design S.C.) ጋር በፈጸመው የማማከር አገልግሎት ውል መሰረት ብር 1,857,181.90 ክፍያ መፈጸም ሲገባው ኮሌጁ እስከ ሰኔ 30, 2010 ዓ.ም ድረስ ብር 4,025,000.00 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሆኖም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 16 (14) (5ለ) መሰረት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል ጊዜው በመራዘሙ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአስራ አምስት በመቶ (15%) የበለጠ መሆን እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም ኮሌጁ ለአማካሪው የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብር ብር 2,167,818.10 ተጨማሪ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ተጨማሪ ክፍያው ከመጀመሪያው ውል ብር 1,857,181.90 ጋር ሲነጻጸር በ116.7% የጨመረ መሆኑ፣

3. በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(11) በአዋጁ አንቀጽ 51(1ሰ) እና 51(2) መሰረት ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ የውል ሥምምነት መፈረም እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም ኮሌጁ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ በተጨማሪነት ለፈጸመው ክፍያ ብር 2,167,818.10 የተጨማሪ የማማከር ሥራ ውል ሥምምነት ያልቀረበለት መሆኑ፤

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

5.4.2. ሥጋት

- ☞ በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ ለተጨማሪ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ይችላል።
- ☞ ከውል በላይ ክፍያን መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

5.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያው ከተፈቀደው በላይ ለተጨማሪ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል በኮንስትራክሽን ክፍያ አፈጻጸሙ ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን።

5.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተጨማሪ ውል ስምምነት ለመፈፀሙ ማስረጃ እንዲቀርብ ለኮንስትራክሽን አማካሪ ድርጅቱ በደብዳቤ ተጠይቋል።

6. ንብረት

6.1. ለመዝናኛ ክበቡ በብድር ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ሸቀጣ ሸቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች፤

6.1.1. ግኝት

በኮሌጁ ለሚማሩ ተማሪዎች ምግብ ለማዘጋጀት የሚውሉ ግብአቶች ለታለመለት አላማ የሚውሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ለተማሪዎች የምግብ እቃ ግምጃ ቤት ሚኒ እስቶር (Mini Store) እና ወፍጮ ቤት ገቢ ከሆኑት ውስጥ በጠቅላላው ዋጋቸው ከብር 203,495.00 በላይ የሆኑ ሸቀጣ ሸቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በሞዴል 22 ወጪ ተደርገው በራሱ ገቢ ለሚንቀሳቀሰው ለኮሌጁ የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ (Cafeteria) በብድር የተሰጡ ቢሆንም ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)

6.1.2. ሥጋት

በብድር የተሰጡት ሸቀጣ ሸቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በወቅቱ ተመላሽ የማይደረጉ ከሆነ፡-

- የመንግሥት በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም።
- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

6.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በብድር የተሰጡት ሸቀጣ ሸቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረጉ እናሳስባለን።

6.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተቋሙ ውስጥ ለተማሪዎች ምግብ አቅርቦት የሚውሉ ግብአቶች የሚቀርቡት አገር አቀፍ ጨረታ በማወዳደር አሸናፊ ከሆኑ ድርጅቶች

ጋር ውል ላይ በተመሰረተ ሥምምነት እንዲያቀርቡ የሚደረግ ሲሆን ይህ ሥምምነት አልፎ አልፎ በተለያዩ ነጋዴዎች በሚያቀርቧቸው ችግሮች እንዲሁም አገር አቀፋዊ በሆኑ ምክንያቶች አቅርቦቱ የሚስተጓጎልበት ሁኔታ ሲፈጠር ተማሪዎችን የመመገብ ኃላፊነት የኮሌጁ በመሆኑ ከመዝናኛ ክበቡ ላይ በተለይም በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከመዝናኛ ክበቡ የምግብ ግብዓቶች በብድር የሚወሰድበት ሁኔታ አለ። በሌላ በኩል የመማር ማስተማሩ በጤናማ አካሄድ እንዲመራ በአብዛኛው ለመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አግልግሎት የሚሰጠው ክበብ አንዳንዴ የገበያ አቅርቦቶች በማይመቻቸበት ወቅት የምግብ ጥሬ እቃ ከተማሪዎች ምግብ ቤት በብድር መወሰዱ ግድ የሚሆንበት ወቅት ይፈጠራል። ከዚህ አንጻር በብድር የመደጋገፍ ሁኔታ በሁለቱም ምግብ ቤቶች ያለ ሁኔታ ነው።

ስለሆነም ከተማሪዎች ምግብ ቤት በ2008 ዓ.ም ብር 203,495.00 የሚያወጡ የምግብ ጥሬ እቃዎች የተወሰደ ቢሆንም በእንጻሩ ለዚሁ የትምህርት ዘመን ከሰራተኞች መዝናኛ ክበብ ብር 135,675.52 የሚያወጡ የምግብ ጥሬ እቃዎች በብድር ለተማሪዎች ምግብ ዝግጅት አገልግሎት እንዲውል ተሰጥቷል። ቀሪው ብር 67,820.00 በ2010 የትምህርት ዘመን ሊመለስ እንደሚችል እንገምታለን።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መደጋገፍ እስካለ ድረስ የእቃዎች ውሰት በተሻለ የቁጥጥር ሥርዓት እንዲፈጸም የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

6.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

መዝናኛ ክበቡ የምግብ ግብዓቶችን በብድር ለተማሪዎች ምግብ ቤት ለመስጠቱ ተጨባጭ ማስረጃ አልቀረበም። ከዚህም በተጨማሪ ብድር በሚሰጥበትና ተመላሽ በሚደረግበት ጊዜ በተጨባጭ የጽሁፍ ማስረጃና ፊርማ መደገፍ ይኖርበታል።

6.2. በብድር የተሰጠ ሰንጋዎች፣ በጎችና የእርባታ እንስሳትን በተመለከተ፤

6.2.1. ግኝት

ኮሌጁ ብር 184,923.00 የሚያወጡ ለሽያጭ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ እንስሳቶችንና የእንስሳት ውጤቶችን ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ

በተለያዩ ጊዜያት ለኮሌጁ የሰራተኞች ክበብ (ካፍቴርያ) በዱቤ የሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል።

(ዝርዝሩ በአባሪ 9 ተያይዟል)

6.2.2. ሥጋት

በብድር የተሰጠው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ ካልተደረገ፡-

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል።
- ☞ በንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

6.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በብድር የተሰጡት ሰንጋዎች፣ በጎችና የእርባታ እንስሳት ገንዘብ በአስቸኳይ ተመላሽ መደረግ አለበት፤ ለወደፊቱም ኮሌጁ በብድር የሚሰጠውን ንብረት በወቅቱ ተከታትሎ ማስመለስ ይኖርበታል።

6.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ኮሌጁ ከአካባቢው ከተሞች ወጣ ብሎ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉንም አገልግሎት ከእራሱ ብቻ የሚያገኝ በመሆኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት ሲባል ለኮሌጁ አካዳሚክና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በብቸኝነት አገልግሎት የሚሰጠው የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ ከመንግሥት በጀት የማይበጀትለትና የሚሰጠውም አገልግሎት ሊቋረጥ ስለማይችል እና ሰራተኞችም ሥራቸውን በተረጋጋ መንፈስ ማከናወን እንዲችሉ ኮሌጁ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ስለሚጠበቅበት ክበቡ የገንዘብ አቅም ውስንነት ስላለበት የኮሌጁን ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በዱቤ ሽያጭ እንዲጠቀምና በመጨረሻም የምርቶችን ዋጋ ክፍያ እንዲፈጸም በማድረግ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ሁኔታዎች አስገድደዋል። በመሆኑም ክበቡ ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ ባጋጠመው የገንዘብ እጥረት ክፍያውን በወቅቱ መክፈል ባይችልም የሚፈለግበትን የዱቤ ክፍያ ለመፈጸም ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል።

6.3. <u>መሥሪያ ቤቱን ከለቀቁ ሰራተኞች ተመላሽ ያልተደረገ ንብረት ስለመኖሩ፤</u>

6.3.1. <u>ግኝት</u>

በኮሌጁ ይሰሩ የነበሩ ሠራተኞች ሥራ በሚለቁበት ወቅት ለሥራቸው የሚያገለግሉ በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) የተረከቧቸውን ቋሚ ዕቃዎች ለንብረት ክፍል ተመላሽ ያደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. አምስት ሰራተኞች ከሥራ ሲለቀቁ የተረከቡትን ቋሚ እቃዎች ያላስረከቡ መሆኑ፤ (ለዝርዝሩ አባሪ 10 ተያይዟል)
2. በአስር መምህራን እጅ ላይ ለሚገኙ ንብረቶች የመቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ያልተዘጋጀላቸው በመሆኑ በሰራተኞቹ እጅ ንብረቶች መኖራቸውን እና ሰራተኞቹ ኮሌጁን ሲለቁ ንብረቶቹን ተመላሽ ስለማድረጋቸው ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
   (ለዝርዝሩ አባሪ 11 ተያይዟል)

ታውቋል፡፡

6.3.2. <u>ሥጋት</u>

1. ሰራተኞች ከሥራ ሲለቁ በእጃቸው ላይ ይገኝ የነበረውን ቋሚ እቃዎች በወቅቱ እንዲያስረክቡ ካልተደረገ፡-
   - ☞ በክትትልና በቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡
   - ☞ የመንግሥት ንብረት ተመላሽ ሳይደረግ ሊቀር ይችላል፡፡
2. በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች በሙሉ መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ካልተዘጋጀላቸው በክትትልና በቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

6.3.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ✓ ኮሌጁ የመንግሥት ንብረት ገቢ እንዲሆን አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች በሙሉመቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

6.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ኮሌጁ ቀደም ሲል ለቋሚ ሰራተኞች የንብረት ርክክብ የሚፈጽመው በቋሚ የንብረት መረካከቢያ ቅጽ (ሰነድ) በመጠቀም ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በነፍስ ወከፍ ካርድ ለመጠቀም አስፈላጊውን የሰነድ ሕትመት በመፈጸም ወደ ነፍስ ወከፍ ካርድ (User Card) በማዞር የምዝገባ ሥራውን ጀምረናል። በመሆኑም በአባሪው ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 እና ከተራ ቁጥር ከ1 እስከ 10 ድረስ የስም ዝርዝራቸው የተጠቀሱ ሰራተኞችና መምህራን ቀደም ብሎ ንብረቶቹን የተረከቡት በቋሚ የንብረት መረካከቢያ ቅጽ (ሰነድ) በመሆኑና ሲሄዱም በዚሁ ሰነድ በመጠቀም ያስረከቡ በመሆኑ የንብረት ርክክብ አፈጻጸም በነፍስ ወከፍ ካርድ ሰነድ ላይ ሊታይ አልቻለም። ስለሆነም የተጠቀሱት ሰራተኞችና መምህራን ቀደም ሲል የተረከቧቸውን ንብረቶችን በስማቸው ከታተመው የስም ቲተር በስተቀር ቀደም ሲል በስማቸው የተረከቧቸውን የመንግሥት ንብረቶችን ሙሉ በሙሉ በአግባቡ ርክክብ በመፈጸም የሄዱ መሆኑን በእርግጠንነት እያረጋገጥን በቀጣይ የሁሉንም ሰራተኞች የንብረት ርክክብ ወደ ነፍስ ወከፍ ካርድ (User Card) በመቀየር በመመዝገብ የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን።

6.3.5. የኦዲተሩ አስተያየት

በተሰጠው ምላሽ መሰረት ንብረቶቹ ተመላሽ ለመሆናቸውና ምዝገባውም የተስተካከለ ለመሆኑ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።

6.4. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በተመለከተ፤

6.4.1. ግኝት

የኮሌጁን የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. **በኮንስትራክሽን ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤**

   1.1. ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

1.2. 58 ፓኬት 3/12 የሆነ ቪቴ፣ 3 የጋሪ እግር፣ 45 ባለ 3 ጣት መኮትኮቻ፣ 15 በመጠን የሚለያዩ አልቪሎች (የብረት መቀጥቀጫ)፣ 400 ሜትር የኢንተር ኮም እና 300 ሜትር የማይክ ኬብል ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.3. 941 ፍሬ ሲንግል ብራኬት የእንጨት ማስነከሻ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.4. 45 ፓኬት ረጅም የአልጋ ጋንች ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.5. 68 እስኳድራ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው መገኘታቸው፤

1.6. 11 ሴራሚክ የሶፍት መስቀያ፣ 2 የሽንት ቤት እና 2 የሻወር ሲንክ፣ 7194 የተለያየ መጠን ያላቸው እርበር ካፕ፣ 6 ያገለገሉ ጉጠት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.7. ከ400 በላይ የሚሆን አጭር የአልጋ ጋንች፣ 33 ፓኬት ባለ10 እስክሮ፣ ከ 2480 በላይ የሚሆኑ ትንሿ የሳጥን ማጠፊያ፣ 73 ፓኬት አንድ ሙሉ ¼ በሰባት የሆነ ቪቴ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.8. 7 የብረት ሞርሳ፣ 10 በሁለት ሰው እና 10 በአንድ ሰው የሚያዝ የእንጨት መቁረጫ መጋዝ፣ 60 የእንጨት ማህሌት (መዶሻ)፣ 3 ሽብልቅ (ድንጋይ መፍለጫ) ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.9. 2ጂ- ክለምን፣ 5 ዌልዲንግ ክላፕ፣ ከ45 በላይ የሚሆኑ የተለያ መጠን ያላቸው መፍቻዎች፣ 22 አካፋ፣ 71 የወርክ ሾፕ መጋዝ፣ 176 ሞለድ እና 324 መጋዝ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.10. 17 የቁም ማጭድ፣ 3 Hand Dril፣ 16 የተሽከርካሪ ወንበር እግር፣ 48 ባለ 3ጣት ዶማ፣ 60 ባለ 125 እና 24 ባለ 160 ካስትል ጎማ፣ 116 ሁክ (መቆፈሪያ)፣ 193 ያገለገሉ ባለ አንድ ጣት ዶማ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.11. 10 Genber Corerers ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.12. 76 የበር ማጠፊያ (Hinges 3 Hole) ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.13. 269 ሬክ መቧጠጫ እና 394 ገሶ (መሬት መቆፈሪያ) ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.14. የተለያዩ ሰነዶች ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.15. የተበላሹ ሁለት ባለ 8 ችቡድ በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.16. 5 ወጪ የሆኑ ላሚራዎች ከ 4ወር በላይ በግምጃ ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

2. በተማሪዎች ምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

3. በነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ግምጃ ቤት በርካታ በገበሬዎች ሁለገብ ማሰልጠኛ ጽሕፈት ቤት ስም የታተሙ ደረሰኞች፣ የምስክር ወረቀቶችና የተለያዩ ሰነዶች ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4. <u>በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

4.1. አምስት 1000ML፣ ስድስት 50ML፣ አራት 100ML፣ ሶስት 500ML በድምሩ 18 ቤከሪ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.2. 9 Valumatics 250ML፣ 84 Valum tube 1ML፣ 1 Pestle & Morese፣ 30 Pepates of 5ML፣ 1 Flascs of 500ML፣ 4 Grind Silinder 250ML፣ 1 White Stem 100ML፣ 1 Beanch Vise፣ 1 Major Jar 2000cc፣ 2 Gest Sprice፣ 3 Grand Celender 500cc & 4 Grand Celender 400cc፣ 8 Explonation Compas እና 2 Reac stro Machine ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.3. 2 ቴምራ የስህል ቀለም እና 6 የዘይት ቀለም ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.4. 7 ኢንች ጄት 45 ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.5. 7 የፎቶ ኮፒ ቶነር ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.6. 3 ዚፕ ዲስክ፣ 1 ሚዲየም ኢንተርቫል ላይት፣ 2 PC Toner NP 1010፣ 3 Scren Fieter 17 ench፣ 10 Screne Projection for tab፣ 50 Film Phoma፣ 3 Spayeral wepe፣ 6 Mirror Sterco Scop፣ 18 Rapido Graph tech pens፣ 5 Plastic Scraper እና 7 Soil Thermo meter ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.7. ከሁለት መደርደሪያ በላይ የላብራቶር ዕቃዎች ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.8. 3T- Square ማስመሪያ ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4.9. የአንዱ ዋጋ ብር 70 የሆነ 160 ቲሸርት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

5. የተሽከርካሪ መለዋወጫ ተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤

6. <u>**የእንስሳት መድሃኒት ግምጃ ቤት**</u>፤

6.1. ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

6.2. በርክክብ ቅጹ ላይ ርክክቡ የተደረገበት ቀን ያልተጻፈ መሆኑ፤

6.3. በግምጃ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈበት መድሃኒቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

7. <u>**የእንስሳት መድሃኒት ሚኒ እስቶር**</u>፤

7.1. ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

7.2. በግምጃ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈበት መድኃኒቶች ተቀምጠው መገኘታቸው፤

7.3. በርካታ ያገለገሉ ዕቃዎች ከሁለት ዓመት በላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

7.4. በግምጃ ቤቱ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤

8. በእንስሳት መኖ በማቀነባበሪያ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈባቸው (የተበላሹ) መኖ(ፍሩሽካ) ካልተበላሹ መኖዎች ጋር አንድ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

9. **<u>የጥጆች በረትን በተመለከተ</u>፤**

9.1. **በበረቱ በር ላይ የሚገኘው የእግር መንከሪያ ኬሚካል** (Phoot Path) **የተበላሸ መሆኑ፤**

9.2. **በበረቱ የሚገኘው የጥጆቹ መመገቢያ ባልዲ ከመበላሸቱ የተነሳ ለጥጆቹ አመቺ አለመሆኑ፤**

9.3. **የጥጆቹ መውጫና መግቢያ በር የተገነጠለና በእንጨት ተደግፎ የቆመ መሆኑ፤**

9.4. **በረቱ ጽዳቱ ያልተጠበቀ መሆኑ፤**

10. **<u>የወተት ማቀነባበሪያን በተመለከተ</u>**

10.1. 1 **ትልቅ ዲፕ ፍሪጅ፣** 2 **ረጃጅም ፍሪጆች እና** 1 **ዲፕ ፍሪጁን የሚያንቀሳቅስ የኤሌክትሪክ ማሽን ለበርካታ ዓመታት ያለምንም አገልግሎት በማቀነባበሪያው ውስጥ ተቀምጠው መገኘታቸው፤**

10.2. **የማቀነባበሪያው ክፍል የውሃ ፍሳሽ መስመር የተበላሸ መሆኑ፤**

11. **የተማሪዎች ጤና ጣቢያ መድሃኒት ግምጃ ቤት ውስጥ** 57 First Aid Kit፣ 5 Delivery Kit፣ 9 Phyesitian Kit፣ 2 Shever፣ 4 Cellona (6*3%)፤ 6 Cellona (10*275) ፣ 3 **ሲሊንደር፣** 4 **የድሮ ሞዴል ማይክሮስኮፕ ከ**1989 **ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤**

12. **የተማሪዎች ጤና ጣቢያ መድሃኒት ሚኒ እስቶር በግምጃ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈበት መድሃኒቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤**

ታውቋል።

6.4.2. <u>*ሥጋት*</u>

ኮሌጁ መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ፡-

- ***ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል።***

☞ የመንግሥት ንብረት ለብክነትና ለብልሽት ሊጋለጥ ይችላል።

6.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ተጠግነው እገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ንብረቶች እንዲጠገኑ፤ መጠገን የማይችሉት ደግሞ መንግሥት ባወጣው የንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ እንዲሁም የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከልና እንዲፈጸም ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው ሥራ መሰራት ይኖርበታል።

6.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. **የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤**

1.1. ግምጃ ቤቱ ስፋት ያለው በመሆኑ ምክንያት ቢን ካርዱ ከዕቃዎቹ ጋር አብሮ ቢቀመጥ ለአቧራ ተጋልጦ ሊበላሽ ይችላል በሚል ግንዛቤ ለብልሽት ሊዳረግ በማይችል ሁኔታ ለቢን ካርዶቹ ቦክስ ፋይል ተዘጋጅቶላቸው በቦክስ ፋይል ውስጥ በጽህፈት ቤቱ ውስጥ በማስቀመጥ ስቶክ የማቀናነሱ ሥራ የሚሰራበት አሰራር በመሆኑ በቀጣይ ለተጠቀሰው ችግር መፍትሄ በማድረግ እንዲስተካከል ይደረጋል።

1.2. ከተራ ቁጥር 1.2 እስከ 1.12 በኮሌጁ እንጨትና ብረታ ብረት ወርክሾፕ ውስጥ የተለያዩ የመኖሪያ ቤት ቁሳቁሶችንና የተለያዩ የቢሮ እቃዎችን እያመረተ በሽያጭ በማቅረብ ለኮሌጁና ለአካባቢው መሥሪያቤቶችና ማኅበረሰብ አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ለምርት ውጤቶች መሥሪያ አገልግሎት ዓላማ እንዲውሉ የተገዙ በመሆናቸውና በኮሌጁ ውስጥ ለሥልጠናው አጋዥ ለጥገና አገልግሎት ከመስጠት በስተቀር በወርክሾፕ ምርት ክፍል የተለያዩ እቃዎች ማምረት ሥራ እንዲቀርና ለሥልጠና ዓላማ ብቻ ትኩረት እንዲደረግ በመደረጉ እና ለምርት ማምረት ሥራ ተገዝተው የነበሩት ጥሬ እቃዎች ሊተርፉ ችሏል። ሌሎችም የተለያዩ ብረታ ብረቶችም ቀደም ሲል ለአርሶ አደሮች የተለያዩ የዕደ ጥበብ ሙያ ሥልጠና በሚሰጥበት ወቅት ለትምህርት መርጃ አገልግሎት

በዕርዳታ የተሰጡና እንዲሁም ሌሎች በሰልጣኝ ተማሪዎች የተመረቱ ምርቶች ናቸው። በመሆኑም ቀደም ብሎ ንብረቶችን በመለየት በተለያዩ የማስወገጃ ዘዴዎች በመጠቀም ከንብረትነት ለማስወገድ እየሰራን ስለሆነ በቅርቡ መፍቴሄ የሚያገኙ ናቸው።

1.3. በተራ ቁጥር 1.13, 1.14, 1.16, በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተጠቀሱ የተለያዩ ሰነዶችን ለማስወገድ እንዲቻል አወጋገዱን አስመለክተው ጉዳዩ የሚመለከተውን አካል የጠየቅን በመሆኑ በመመሪያው መሰረት በቅርቡ እንዲወገዱ ይደረጋል።

1.4. በተራ ቁጥር 1.15 የተጠቀሰው ዕቃ ቀደም ሲል ወጪ ያደረገው የሥራ ሂደት በመውሰድ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርገዋል። በቀጣይ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም እርምት ይደረጋል።

2. <u>በቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት</u>፤

2.1. በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከተራ ቁጥር 4.1 እስከ 4.8 ድረስ የተጠቀሱ ንብረቶች ቀደም ሲል ለትምህርት መርጃ አገልግሎት እንዲውሉ በእርዳታ የተሰጡ ሲሆን ይሰጡ የነበሩት የሥልጠና ዓይነቶች በመቀየራቸው እና አዲስ ለተፈጠሩ ሥልጠናዎች ደግሞ አገልግሎት ሊውሉ የማይችሉ በመሆናቸው ምክንያት የተረፉ ናቸው። በመሆኑም ለኮሌጁ ምንም አገልግሎት የማይሰጡትን በመለየት በቅርቡ ከንብረትነት እንዲወገዱ ይደረጋል።

2.2. በተራ ቁጥር 4.9 የተመለከተው በቁጥር 160 የሆኑ ቲ ሸርቶች በኮሌጁ ውስጥ ለተቋቋመው ለሥርዓተ ጾታ ክለብ ዓላማ አገልግሎት እንዲውሉ የተገዙና የተረፉ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ወጪ ሆነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

3. በተሽከርካሪ መለዋወጫ ተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ ሲሆን በቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ እንወስዳለን።

4. <u>**የእንስሳት መድኃኒት ግምጃ ቤት**</u>፤

በተራ ቁጥር 6.1 **እና** 6.2 **በተጠቀሱት ላይ በቀጣይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃ እንወስዳለን። በተራ ቁጥር** 6.3 **የተጠቀሱት ደግሞ ከንብረትነት እንዲወገዱ ጥያቄ የቀረበባቸው በመሆኑ በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል።**

5. <u>**የእንስሳት መድኃኒት ሚኒ እስቶር**</u>፤

በተራ ቁጥር 7.1 **እና** 7.4 **በተጠቀሱት ላይ በቀጣይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃ እንወስዳለን። በተራ ቁጥር** 7.2 **እና** 7.3 **የተጠቀሱት ደግሞ ቀደም ብሎ ከንብረትነት እንዲወገዱ ጥያቄ የቀረበባቸው በመሆኑ በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል።**

6. **በእንስሳት መኖ በማቀነባበሪያ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈባቸው** (**የተበላሹ**) **መኖ**(**ፍሩሽካ**) **ካልተበላሹ መኖዎች ጋር አንድ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ ሲሆን ከንብረትነት እንዲወገዱ ጥያቄ የቀረበባቸው በመሆኑ በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል።**

7. <u>**የጥጆች በረትን በተመለከተ**</u>፤

በተራ ቁጥር 9.1, 9.3 **እና** 9.4 **በተጠቀሱት ላይ በቀጣይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃ እንወስዳለን። በተራ ቁጥር** 9.2 **የተጠቀሰው ደግሞ ቀደም ብሎ በበጀት እጥረት ምክንያት ያልተገዛ በመሆኑ በ**2010 **በጀት ዓመት የሚገዛ በመሆኑ ችግሩ ይቀረፋል።**

8. <u>**የወተት ማቀነባበሪያን በተመለከተ**</u>፤

በተራ ቁጥር 10.1 **የተጠቀሱት ዕቃዎችም ባይሰሩም ተማሪዎች በአካል አይተው ለተግባር ትምህርት መማሪያ አገልግሎት እንዲውሉ ስለሚፈለጉ ነው። በቀጣይ በአዲስ ዕቃዎች ሲተኩ ከንብረትነት እንዲወገዱ ይደረጋል። በተራ ቁጥር** 10.2 **በተጠቀሰው ላይ በቀጣይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃ እንወስዳለን።**

9. **በተራ ቁጥር** 11 **እና** 12 **በተጠቀሱት ላይ ቀደም ብሎ እንዲወገዱ ጥያቄ የቀረበባቸው በመሆኑ በቅርቡ ከንብረትነት እንዲወገዱ ይደረጋል።**

6.4.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ኮሌጁ በንብረት አስተዳደሩ ላይ የተገለጹ ክፍተቶችን ለማስተካከል እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ሲሆን እርምጃ ተወስዷል ተብለው የተሰጡት ምላሾች አግባብነትና ትክክለኛነት በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጡ ይሆናል። ሆኖም ኮሌጁ የጀመረውን ጥረት በማጠናከር የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከልና እንዲፈጸም ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው ሥራ መሰራት ይኖርበታል።

7. በጀት

7.1. በሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

7.1.1. ግኝት

ለኮሌጁ ለ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የውስጥ ገቢ በጀትና ካፒታል የወጪ በጀት በሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

- ✓ ከካፒታል በጀት ብር 4,659,470.25፣
- ✓ ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 6,031,771.77 ፣

በድምሩ ብር 10,691,242.02 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 12 ተያይዟል)

7.1.2. ሥጋት

- ☞ የወጪ ሂሣብ በጀቱ በእቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።
- ☞ በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

7.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ

ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

7.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. መደበኛና ካፒታል በጀት

☞ በ2009 በጀት ዓመት ከተፈቀደልን በጀት ውስጥ በአብዛኛው የሚፈለገውን የእቃና የአገልግሎት ግዥ ፈጽመን የቀረ ሲሆን በተወሰኑ የበጀት ኮዶች ላይ ግን የግዥው በጀት የበጀት ዓመቱ ሲጠናቀቅ ጥቂት ቀናቶች ሲቀሩት የተለቀቀ በመሆኑ መጠቀም ያልተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ውስጥ በእያንዳንዱ የበጀት ኮድ ላይ አጠቃቀማችንን የሚገልጽና ያልተጠቀምንበትን ምክንያት የሚገልጽ ሰንጠረዥ በ2009 በጀት ዓመት ከወጪ ቀሪ ቆጠራ ሪፖርት ማብራሪያ በገለጽንበት ወቅት ለማስተባበሪያው ጽህፈት ቤት አሳውቀናል፡፡

☞ ሌላው በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተፈቀደልንን በጀት በአግባቡ እንዳንጠቀም ተጽዕኖ ካሳደረብን ውስጥ በግዥ የሥራ ሂደት ባለው የሰው ኃይል እጥረት የተነሳ የጨረታ ውጤቶች በወቅቱ ለአቅራቢዎች በወቅቱ ባለመገለጹ እና የሥራ ውል ሥምምነት ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ግዥው ሳይፈጸም የቀረ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2. የውስጥ ገቢ በጀት

በበጀት ዓመቱ ይገኛል ተብሎ በአብዛኛው በሰብል ልማት የተያዘው የምርት ሥራ በገጠመን የአየር ንብረት ለውጥ የተጠበቀውን ያህል ገቢ ባለማግኘታችን የተነሳ በተለያዩ የበጀት ኮዶች ላይ በተፈለገው ልክ ግዥ ያልተፈጸመ እና ያልተጠቀምንበት መሆኑን እንገልጻለን፡፡

7.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

1. ኮሌጁ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል

በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው *መሥሪያ* ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ማስተባበሪያው ጽህፈት ቤትና ሚኒስቴር *መሥሪያ* ቤቱ እንዲያውቁት እንዲደረግና በዚያው በኩል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያውቀው መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

2. በበጀት ዓመቱ ከውስጥ ገቢ ይገኛል ተብሎ የተያዘው በጀት በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ገቢውን ለመሰብሰብ የማይቻል ከሆነ ሁኔታውን በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ማስተባበሪያው ጽህፈት ቤትና ሚኒስቴር *መሥሪያ* ቤቱ እንዲያውቁት እንዲደረግና በዚያው በኩል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያውቀው መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

8. ልዩ ልዩ

8.1. በ2008 በጀት አመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶችን በተመለከተ፤

8.1.1. ግኝት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር *መሥሪያ* ቤት የ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ኮሌጁ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ንብረት

- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ ሃያ ስድስት (26) ፍሪጆች፣ አንድ የውሃ ሞተር ፓምፕ፣ ሁለት ጄነሬተሮች፣ ወንበሮች፣ በርካታ ኮምፒዩተሮች፣ ታይፕ ራይተር፣ ፕሪንተሮች እንዲሁም የፎቶ ኮፒ ማሽኖች በስቶር ውስጥ ያለአገልግሎት የሚገኝ መሆኑ፤
- ✓ የኮሌጁ ላይብረሪ እየፈራረሰ መሆኑ፤

- ✓ በኮሌጁ ያሉት ከብቶች ከኮሌጁ ውጪ ካሉት ከብቶች ጋር የሚገናኙ መሆኑ፤

2. **<u>ተሽከርካሪ</u>**

- ✓ ሁለት ሞተር ሳይክሎች (የሰሌዳ ቁጥር 4-0075 እና 4-0375) ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤
